ላንቺና ለልጆችሽ የሚበቃሽን ከገንዘቡ በአግባቡ ውሰጂ!" አሏት።

ከአማኞች እናት ዓኢሻ ረዲየሏሁ ዐንሃ - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - እንደተላለፈው እንዲህ አለች: «የአቡ ሱፍያን ባለቤት የሆነችው ሂንድ ቢንት ዑትባ የአላህ መልክተኛ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- ዘንድ
ገባችና እንዲህ አለች: "የአላህ መልክተኛ ሆይ! አቡ ሱፍያን ንፉግ ሰው ነው። ሳያውቅብኝ ከገንዘቡ ካልወሰድኩ በቀር ለኔና ለልጆቼ የሚበቃንን ወጪ አይሰጠኝም። በዚህ እኔ ላይ ወንጀል ይኖርብኛልን?" የአላህ መልክተኛም ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና
ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- "ላንቺና ለልጆችሽ የሚበቃሽን ከገንዘቡ በአግባቡ ውሰጂ!" አሏት።» [ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ሂንድ ቢንት ዑትባ ረዲየሏሁ ዐንሃ - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - ስለባሏ አቡ ሱፍያን ረዲየሏሁ ዐንሁ - አላህ መልካም ሥራውን ይውደድለትና - ነቢዩን ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- ጠየቀች። እርሱ በገንዘቡ ስስታምና ንፉግ ነበር። እርሱ ሳያውቅ በድብቅ ከገንዘቡ ካልወሰደች በቀር ለርሷና ለልጆቿ የሚበቃትን ወጪ አይሰጣትም ነበር። ይህን በማድረጓ ወንጀል ይኖርባት እንደሁ ጠየቀች። ነቢዩም ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- "ባያውቅ እንኳ በተለምዶ በቂ ነው ተብሎ የተለመደውን ያህል ላንቺና ለልጆቹ ከገንዘቡ ውሰጂ።" አሏት።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/2965